
# ምክትል ጠ/ሚ አቶ ደመቀ መኮንን ከመፈንቅለ መንግስቱ በስተጀርባ የሉም ማለት ይቻላልን?

**************************



"መፈንቅለ መንግስት ወይስ መንግስታዊ ወንጀል" በሚል ርእስ በያሬድ ጥበቡ የተፃፈውን አነበብኩት፡፡ ትንታኔው፣ የማስረጃዎች ቅንብር እና አሰካክ በጣም ሀሪፍ እና አሳማኝ ነው፡፡ ፀሃፊው ምክትል ጠ/ሚ ደመቀ መኮንን ኤርፖርት እያሉ ለምን አልተነገረም፣ በሚል አንኳር ነጥብ መንግስታዊ ወንጀል ነው ብሎታል፡፡

በኔ እምነት መንግስታዊ ወንጀል ሳይሆን መፈንቅለ መንግስት ነው፡፡ ነገር ግን መፈንቅለ መንግስት ሲባል ምክትል ጠ/ሚ ወይም ዋናው ጠ/ሚ እንዳሉት ኣይደለም፡፡ ይህ ከማብራራቴ በፊት ግን ስለ ያሬድ ጥበቡ ፅሁፍ አንድ መሰረታዊ ነጥብ ልጣል፡፡

ያሬድ ጥበቡ ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ ሲነሳሳ አንድ መሰረታዊ ሓቅ የዘነጋ በመሆኑ ጠቅላላ ትንታኔው ውድቅ ያደርገዋል፡፡ እሱም፡-

ከአዲስ አበባ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ የሚደረግ በረራ ከ14 ሰዓት ያላነሰ ነው፡፡ ስለዚህ አቶ ደመቀ መኮነን ወደ አሜሪካ የተጓዙት ቅዳሜ ማታ ሳይሆን ምናልባት ዓርብ ሌሊት መሆን አለበት ምክንያቱ ቅዳሜ ምሽት 5 ሰዓት አከባቢ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከዋሽንግቶን ዲሲ በስልክ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ ይህ መልእክት ተመስገን በየነ ባወጀው ዜና እኔ ራሴ ሰምቸዋሎ፡፡ የአውሮፕላኑ ጉዞ ከ14 ሰዓት ያላነሰ ነው ካልን አቶ ደመቀ መኮንን ትራጀዲው በሚጀመርበት ጊዜ አየር ላይ ወይም አውሮፕላኑ ዋሽንግቶን ዲሲ አርፎ ኤርፖርት ላይ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚ በዚህ ብቻ ሁሉ ትንታኔ ፉሩሽ ያደርገዋል፡፡ ይህ ስል ምክትል ጠ/ሚ ከደሙ ወይም ከሴራው ንፁህ ናቸው ለማለት አይደለም፡፡ አቶ ያሬድ ጥበቡ ያደረገው ትንታኔ አልስማማበትም ለማለት እንጂ አቶ ደመቀ አያደርጉትም ከሚል አይደለም፡፡

በኔ እምነት ይህ መፈንቅለ መንግስት የተደረገው በክልል ብቻ የታጠረ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ ክልል ብቻ ለመፈንቀል የሚያስብ ካለ ቀሽም ነው፡፡ ወይም ደግሞ ጀነራል አሳምነው ይህን ድርጊት የፈፀመው ከክልሉ አመራር ስላልተግባባ በስሜት ያደረገው ነው የሚል ካለም እሱም የዋህ ነው፡፡

ታድያ ምንድን ነው ?

ይህን ለመመለስ ትንሽ የኋላ ትእይንት መገንዘቡ አስፈላጊ ነው፡፡

ቲም ለማ ስልጣን ሲይዝ በትክክለኛ የኢህአዴግ ወይም የተራማጅ ድርጅት አካሄድ ተከትሎ አይደለም፡፡ ስልጣን የያዘው የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በመበላሸታቸው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ወጥተው ወደ ጥገኛ ጎራ ስለተቀላቀሉ ነው፡፡ በመሆኑም በኢህአዴግ ውስጥ ስውር ቡድን /የኦሮማራ ቡድን/ በመመስረት ስልጣን ተቆጣጥረዋል፡፡ ይህ ሲደረግ ግን እነዚህ ድርጅቶች ማለትም ብአዴን እና ኦህዴድ ሴራውን ሲያሴሩ ከችግራቸው ወጥተው ታድሰው እና ንፁህ ሆኖው ሳይሆን ይህ ሴራ ያሴሩት በመበስበሱ በሽታ ሩቅ ርቀት ከተጓዙና ሙሉ ለሙሉ በጥገኞች ጎራ ከተቀላቀሉ ነበር፡፡ ሴራውም በህወሓት ላይ በማነጣጠር የኢህአዴግ ስልጣን የመቆጣጠር የጋራ ዓላማ ነበር፡፡ ስለሆነም በ2010 ዓ.ም. የተደረጉ የኢህአዴግ ግምገማዎች ሁሉም ፌክ እና ስልጣን ለመያስ የማስመሰል ግምገማዎች ነበሩ፡፡ ስልጣኑም 108 ለ 59 ድምፅ በማሸነፍ ቲም ለማ በድል አጠናቀቀ፡፡ ይህ ቡድን የነበረውን ተልእኮ በዚች የድምፅ አሰጣጥ ቀን በድል ተጠናቀቀ፡፡ በቃ ይህ ቡድን አንድ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡

ምክንያቱ

የኢህአዴግ እህት ድርጅቶችን ያስተሳሰረው አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ነበር፡፡ ነገር ግን አዴፓ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ አያስፈልግም ኣብቅተዋል በማለት አቋም ይዟል፡፡ ይህ ማለትም የብሄር ብሄረሰቦች መብት ብሎ ነገር፣ ፌደራል ስርዓት ብሎ ነገር እንደማይቀበል፣ ህገመንግስቱም የአማራ ህዝብ አልተሳተፈበትም ብአዴን እንደሆነ የህወሓት አሽከር ነበር ብሎ በይፋ መግለጫ ሲሰጥ ታይቷል፡፡ ስለዚ ፍላጎቱ አሃዳዊ ስርዓት ነው፡፡

ኦዴፓም በግላጭ ልማታዊ ዴሞክራሲ አበቃለት ባይልም ግን ደግሞ የልማታዊ ዴሞክራሲ ተፃራሪ የሆኑ ተግባራት ሲፈፅም ይታያል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ በአዲስ አበባ ዙርያ፣ በብሄረሰብ መብት ዙርያ ከአዴፓ የተለየ አቋም ሲይዝ እና መሀል ላይ አስታራቂ ለመምሰል ሲሞክር ይስተዋላል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የአዴፓ እና የኦዴፓ ትስስር ህወሓትን ለማግለል ወይም ከመንግስት ስልጣን ለማስወገድ ብቻ እንጂ ቀጣይ አንድ የሚያደርጋቸው የሚያስተሳስራቸው ስትራቴጂያዊ ዓላማ እንደሌላቸው ነው፡፡

በመሆኑም

ከዚህ ቀጥሎ የሚኖረው ፍልምያ “ሁለት ሌቦች የሰረቁትን ሲከፋፈሉ ይጣላሉ” እንደሚባለው አዴፓ እና ኦዴፓ በስልጣን ክፍፍል፣ በአማራ እና ኦሮሚያ ወሰን ወይም ድንበር ይገባኛል፣ ሲነታረኩ ሲጣሉ መኖር ነው፡፡ ይህም ያለፉት ጥቂት ወራት የነበረውን ሁኔታ ማስታወስ በቂ ነው፡፡

አሁን ደግሞ ወደ አማራው ፅንፈኛ የተቀላቀለው አዴፓ በዚህ የኢትዮጵያ ህገመንግስት ተመስርቶ አሃዳዊ ስርዓት መመስረት እንደማይችል በደንብ ስለተገነዘበ ያለውን ብቸኛ መንገድ መፈንቅለ መንግስት በማካሄድ ኦዴፓን መጣል ነው፡፡ <u>በመሆኑም ይህ በአማራ ክልል ላይ የተፈፀመው የመፈንቅለ መንግስት ሴራ ለአማራ ክልል ብቻ ሳይሆን ለፌደራል ስርዓቱ የታቀደ እና የተቀነባበረ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡</u> ምክንያቱ አሀዳዊ ስርዓት ለመመስረት ብቸኛው መንገድ መፈንቅለ መንግስት በማድረግ ህገመንግስቱን መናድ ነው፡፡ ይህ ለማድረግ ደግሞ ለዚህ ዓላማ መሰናክል ናቸው ያላቸው እና በፌደራል ደረጃ ህገመንግስቱን ለመናድ እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ የተባሉትን በመግደል ማስወገድ ነበር፡፡ ይህም ከፍተኛ ዝግጅት ይጠይቅ ነበር በርካታ ታጣቂ ማሰልጠን እና እስከ ፌደራል መንግስት መስሪያቤቶች የጥፋት ሰንሰለት መዘርጋት ነበር፡፡

*ይህ ለማድረግ በክልል እና በፌደራል መንግስት መዋቅር የሚገኙ የአዴፓ ከፍተኛ አመራች ቀጥተኛ ተሳትፎ ሳይታከልበት በአንድ የክልል ቢሮ ሀላፊ ብቻ የሚመራ ወይም የሚፈፀም የቀሽሞች መፈንቅለ መንግስት እንደማይሆን መረዳት ይቻላል፡፡* ምክንያቱም ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ፅጌ ጠንካራ የደህንነት መዋቅር በነበረበት ወቅት የፈፀሙት የከሸፈው የመፈንቅለ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት የወሰዱ በመሆናቸው እና በአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ላይ የወሰዱት የግድያ እርምጃ ሰዎችን ጥንቃቄ በተሞላበት በመለየት ገሚሱ እገታ ገሚሱ ደግሞ ግድያ ነበር የፈፀሙት፡፡

ሌላው ምክንያት ደግሞ ይህ ትራጄዲ በሚፈፀምበት ወቅት *ምክትል ጠ/ሚ እና ውጭ ጉዳይ ሚ/ር /ሁለቱም የቲም ለማ አባላት እና የአዴፓ ክንፍ/ ከአገር እንዲወጡ መደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ጠ/ሚ እና የመከላከያ ሚ/ር /ሁለቱም የቲም ለማ አባላት እና የኦዴፓ ክንፍ/ አገር ውስጥ መቆየታቸው፣ ሲታይ አዴፓ ልክ ህወሓትን እንዳደረገው ኦዴፓ ላይ ሴራ ማሴሩ ያሳያል፡፡*

ሆኖም ምክትል ጠ/ሚ አቶ ደመቀ መኮነን እንዳሉት *እንዳሰብከው አይሆንም እንደሰጠህ ነው*ና የታሰበው ሴራ ከሸፈ ኢትዮጵያ የታቀደላትን እልቂት በእግዚአብሄር ቸርነት ሳይፈፀም ቀረ፡፡

አዴፓ በህወሓት ላይ ያሴረው ስውር ሴራ በኦዴፓ ሳይፈፅም የሚቆም አይደለም ምክንያቱ አንዴ ከልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር በመውጣቱ ያለው ብቸኛ መንገድ የጥገኞች ወይም የሴረኞች መንገድ ብቻ በመሆኑ፡፡ አዴፓ የሚከተለው የጥገኞች መንገድ ደግሞ አህዳዊ ስርዓት የሚያደርስ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ይህ ህልሙ ደግሞ በዚህ የያዝነው ህገመንግስት መቸም እውን እንደማይሆን ማንም ያውቀዋል፡፡ ስለዚ ይህ ህልሙ እውን ለማድረግ ደግሞ ብቸኛው መንገዱ በመፈንቅለ መንግስት ህገመንግስቱ መናድ ብቻ ነው፡፡

*ስለዚ ምክትል ጠ/ሚ ኣቶ ደመቀ መኮንን፣ ውጭ ጉዳይ ሚንስተር አቶ ገዱ፣ አሁን ያሉ የአማራ ክልል ተጠባባቂ ርእሰመስተዳድር ይሁን ሌላው የአዴፓ አመራር፣ በልማታዊ ዴሞክራሲ ያላቸው አቋም፣ በአህዳዊ ስርዓት ያላቸው አቋም፣ እንዲሁም አህዳዊ ስርዓት ለመገንባት የሚጠቀሙበት ስልት /በመፈንቅለ መንግስት/ ሁሉም ከብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ፅጌ ልዩነት አልነበራቸውም አሁንም የላቸውም፤ ይህም አቋማቸውም በአማራ መገናኛ ብዙሀን በግልፅ አሳውቀዋል፡፡ ልዩነቱ መቼ ይሁን፣ መጀመሪያ ምን እንስራ፣ ቀጥሎ ምን እናድርግ፣ የሚሉ ብቻ ነበር፡፡*

ስለዚህ አዴፓ ህልሙን /አህዳዊ ስርዓት/ እውን ለማድረግ ተከታታይ ግድያዎች እና መፈንቅለ መንግስት የማያደርግበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ይህን የትምክህት ሴራ ተገንዝበው ህገመንግስቱን ከማስከበር አኳያ ሀላፊነታቸው ካልተዋጡ፣ ጦሱ እሳቸው ጋር የማይደርስበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአህዳዊ ስርዓት ናፋቂዎች በጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ዙርያ እያንዣበቡ ይገኛሉ፡፡ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ከዚህ የትምክህት ሴራ መውጣት የሚችሉት ሁለት መንገድ አላቸው

1. አንደኛው አማራጭ ህዝቡ የሰጣቸው ህገመንግስታዊ አደራ አጥብቀው በመያዝ የተሰጣቸው ስልጣን ከህዝቡ ጋር በመሆን ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ማስቀጠል፤
2. ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ከአህዳዊ ስርዓት አቀንቃኝ ትምክህተኞች ድብቅ ሴራ በማሴር በመፈንቅለ መንግስት ስም ስልጣናቸው በማስረከብ ወደተመቻቸላቸው የተደላደለ ቦታ ህዝቡን እና ህገመንግስቱን በመካድ መፈርጠጥ ነው፡፡

ከነዚህ አማራጮች ውጭ ግን የሚጠብቃቸው ዕጣፈንታ የነ ዶ/ር አምባቸው ዕጣ ነው፡፡ ስለዚህ የኔ ምክር የመጀመሪያውን አማራጭ ይዞ በከፍተኛ የህዝቦች ትግል እና መስዋእትነት የመጣውን ህገመንግስት በማክበር እና በማስከበር የበኩላቸውን አሻራ በማኖር የአገራችን የህዳሴ ጉዞ በማስቀጠል ታሪካዊ አደራ እንዲወጡ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በትምክህተኞች ሴራ እንደ ሊብያ ወይም ሶርያ አትሆንም

ህዳሴ ኢትዮጵያ

ሰኔ 29፣ 2011 ዓ.ም.

አስተያየት በሚቀጥለው አድራሻ ማድረስ ይቻላል

hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopia@gmail.com